የሰ/መ/ቁ. 32815

ግንቦት 05/2000

ዳኞች፡- 1. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

2. አቶ ሐጐስ ወልዱ

3. ወ/ት ሂሩት መለሰ

4. አቶ መድሕን ኪሮስ

5. አቶ ሱልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ታፈሰ ጠበቃዋ ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የሺመቤት ትኩ አልቀረበችም

ፍ ር ድ

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው በይርጋ አለም ከተማ መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ የአባታቸው ወራሽ በመሆናቸው ንብረት ተጣርቶ ድርሻቸውን ተጠሪ እንዲያካፈሏቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚልና ሌሎችም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ካቀረቡ በኋላ ለጉዳዩ ሙሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤትም አመልካች ወራሽ መሆናቸውን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ 4 አመት ያለፈው በመሆኑ ክሱ በፍ/ሀ/ቁ. 1000 (1) መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዛም ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቶቹ ይግባኛቸውን ሣይቀበሏቸው ቀርተዋል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ችሎቱ የአመልካች ጥያቄ በፍ/ህ/ቁ. 1000 (1) መሰረት በይርጋ ይታገዳል መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ እና ከክርክሩ እንደተረዳነው የአመልካች አባትና ተጠሪዋ ባልና ሚስት የነበሩ ሲሆን የአመልካች አባት በመሞታቸው ምክንያት አመልካች በወራሽነታቸው የሚገባቸውን የአባታቸውን ድርሻ ተጠሪ እንዲያካፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም የአመልካች አባት የሞቱት ሰኔ 12/1992 ሲሆን ክሱ የቀረበው ግን ሐምሌ 06 ቀን 1998 ዓ.ም በመሆኑ በፍ/ህ/ቁ. 1000 (1) መሰረት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ተጠሪዋ የሚከራከሩበት ድንጋጌ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት አለው ወይ? የሚለውን ነጥብ ይህ ችሎት መርምሯል፡፡

አንድ ሰው ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው ውርሱን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ ያደረገ እንደሆነ እውነተኛ ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተያዘበት ንብረት እንዲመለስለት ለመጠየቅ እንደሚችል ተመልክቷል (የፍ/ህ/ቁ. 999 ይመለከታል) ይህንንም ጥያቄ ለማቅረብ የሚችለበት ጊዜ በፍ/ህ/ቁ. 1000 ሥር ተወስኖ ተቀምጧል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ጉዳይ ለማወቅም ድንጋጌዎቹ የሚገኙበት የፍትሐብሔሩ ክፍል እንዲሁም ድንጋጌዎቹን በራሣቸው ማየት ይጠቅማል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚገኙት ስለውርስና ወራሽነት በሚመለከተው የህጉ ክፍል በመሆናቸው በተጨማሪ ድንጋጌዎቹን በጥሞና ስንመለከታቸውም የክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት ባለቤት ወራሾች ነን በሚሉ ሰዎች መካከል የሚነሣን ክርክር የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ ይህ ችሎት በመ/ቁ. 30078 የሰጠውን ትርጉም

ማየት ይችላል በመሆኑም የፍ/ህ/ቁ. 1000 ተፈፃሚነት የሚኖረው በወራሾች መካከል በሚነሣው የውርስ ንብረት ወይም አውራሽ ክርክር ላይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግን አመልካች የሟች ወራሽ ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ የሟች ሚስት ናቸው ስለሆነም ክርክሩ ወራሽ በሆኑት አመልካችና ወራሽ ባልሆኑት ተጠሪ መካከል የሚደረግ በመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 1000 ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ይልቁኑ ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም "ስለ ወሎች በጠቅላላው" በሚል የተደነገገው የይርጋ ደንቦች ተፈፃሚነት አላቸው (የፍ/ህ/ቁ. 1677(1)) ይመለከታል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ የጠቅላላው የውል ድንጋጌ እንጂ የፍ/ህ/ቁ. 1000 ተፈፃሚነት ስለሌለው የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው በማለታቸው የህግ ሥህተት ፍጽመዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የይርጋ አለም ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13/98 በ18/03/99 የተሰጠውና እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የፀናው ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348 መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካቿ አባት የሞቱት ሰኔ 12/1997 በመሆኑና ክሱ የቀረበውም በ06/11/98 በመሆኑ ጥያቄው በፍ/ህ/ቁ. 1845 መሰረት አልታገደም
3. የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ ለይርጋ አለም ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ